የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፌ ዴ ራ ላ ዊ ዲ ሞ ክ ራ ሲ ያ ዊ ሪ ፐ ብ ሊ ክ

# የ ፌ ዴ ራ ል ጠ ቅ ላ ይ ፍ ር ድ ቤ ት

የሰበር መ/ቁ/ 207000

ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም

**ዳኞች**፡ብርሃኑ አመነዉ

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

**አመልካች**፡ ባልደራስ ለእዉነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ፡- ወኪል ሄኖክ አክሊሉ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፡- ተወካይ አውድሮ ታደሠ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለ6ኛዉ ጠቅላላ ምርጫ አመልካች ያቀረበዉ እጩ ተወዳዳሪ ምዝገባ መከልከሉን በመቃወም አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመልከተዉ የምርጫ ጉዳዮች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በሰበር እንዲታረም የቀረበ ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ለ6ኛዉ ጠቅላላ ምርጫ በተወዳዳሪነት የተመዘገበዉ አመልካች በአ/አ/ከተማ በየካ ምርጫ ክልል በእጩነት እንዲመዘገብ አቶ እስክንድር ነጋ፤በንፋስ ስልክ ላፍቶ ምርጫ ክልል አቶ ስዩም ቸኮል እና በምርጫ ክልል 26/27 ወ/ሮ ቀለብ ስዩም ያቀረበ ቢሆንም በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ስለሆነ በእጩነት ሊመዘገቡ አይችሉም የሚል ዉሳኔ በምርጫ ክልል አስፈጻሚ በመወሰኑ ይህንኑ በመቃወም ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተመሳሳይ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአ/አ ከተማ ምርጫ ቦርድ



ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ
ፊርማ ቀን 17/09/13

ቅ/ጽ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይህንኑ ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ቀጥሎ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ በእስር ላይ የሚገኝ ሰዉ የመንቀሳቀስ መብቱ ወይም ነጻነቱ የተገደበ ነዉ ፣ምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ አይችልም፣ቢመረጥም ህዝቡን ሊያገለግል አይችልም የሚሉ ምክንያቶችን በመስጠት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፣በህግ ጥላ ስር የሚገኙ እጩ ተወዳዳሪዎች በእጩነት መመዝገብ እንዳይችሉ በህግ የተቀመጠ ክልከላ አለመኖሩን፣የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔዉ የሰጠዉ ምክንያት ህጋዊ መሰረት እንደሌለዉ እንዲሁም የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ንጹህ ሆኖ የመገመት መብት እንዳላቸዉ እና የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይህንኑ የሚጻረር እንደሆነ በዝርዝር በመግለጽ ዉሳኔዉ እንዲታረም አመልክቷል፡፡የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በ2013ዓ.ም በሚደረገዉ 6ኛዉ ሐገር አቀፍ ምርጫ አመልካች በእጩነት እንዲመዘገቡለት ያቀረባቸዉ እጩዎች ቀደም ሲል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዉ በፍርድ ቤት ዋስትና ተከልክለዉ በማረፊያ ቤት በመሆናቸዉ ከምርጫ ህጉ ዓላማና አፈጻጸም አኳያ በተመራጭነት ለመወዳደር በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም ተብሎ በአብላጫ ድምጽ በስር ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ከምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 31/1/ሠ አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡

በተጠሪ በኩል ያቀረበዉ መልስ ባጭሩ፣የእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 53/8/ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ እንጂ ሌላ የይግባኝ እርከን ስለመኖሩ የሚያመለከት አይደለም በማለት ለሰበር የቀረበዉ ይግባኝ እንዲሰረዝ የመጀመሪያ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በስረነገር ረገድ አመልካች ያቀረባቸዉ አራቱ እጩዎች በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በወንጀል ተጠርጥረዉ በህግ ጥላ ስር ታስረዉ የሚገኙና የዋስትና መብታቸዉን ተከልክለዉ በማረሚያ ቤት ስለሚገኙ ለምርጫ በእጩነት ተመዝግበዉ በምርጫ ሂደቱ በነጻነት የመንቀሳቀስ እና ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ከመራጩ ህዝብ ጋር በአካልም ሆነ በሚዲያ ሊገናኙ እንደማይችሉ በመገንዘብ የተሰጠ ዉሳኔ መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትንታኔ የህጉን ዓላማ ያገናዘበ ስለመሆኑና አመልካች ያቀረባቸዉ እጩዎች በእስር ላይ አለመሆናቸዉ ማስተባበያ ያልቀረበበት መሆኑን እንዲሁም ቅሬታ በቀረበባቸዉ ምርጫ ክልሎች ሌሎች እጩዎችን ማስመዝገቡን ገልጾ ቅሬታዉ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡



ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
17/09/13

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንድቀርብ የተደረገበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ አመልካች በምርጫ አዋጁ መሰረት ተመዝግቦ ህጋዊ ሰዉነት አግኝቶ ለ6ኛዉ ጠቅላላ ምርጫ ዉድድር እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ አላከራከረም፡፡(የኢትዮጵያ ምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና ምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁ/1162/2011ዓ.ም /ከዚህ በኋላ አዋጅ እየተባለ ይጠቀሳል/ አንቀጽ 66/1/ ይመለከታል፡፡ይሁንና እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ያከራከረዉ ጉዳይ አመልካች በእጩነት እንዲመዘገቡለት ካቀረባቸዉ ሰዎች ዉስጥ በወንጀል ክስ ቀርቦባቸዉ በህግ ጥላ ስር ናቸዉ የተባሉት በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም ተብሎ መከልከላቸዉ አግባብነት ላይ ነዉ፡፡ጉዳዩ ለዚህ ሰበር የቀረበዉ ይህንኑ ጭብጥ ለመመርመር ነዉ፡፡ነገር ግን ይህንን ጭብጥ ከመመርመራችን በፊት ተጠሪ ያቀረበዉ ተቃዉሞ ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ በተጠሪ በኩል የእጩ ምዝገባ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጪ አካል የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 153/8 ከመደንገጉ ዉጪ ሌላ የፍርድ ቤት እርከን ስለመኖሩ በአዋጁ አልተመለከተም በማለት ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ሊያስተናግድ አይገባም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል፡፡ምርጫን አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በዝርዝር ደንግጓል፡፡በዚህ መዝገብ የተያዘዉ ጉዳይ የእጩ ምዝገባ የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ረገድ በአዋጁ አንቀጽ 153 ስር እንደተደነገገዉ በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሰዉ ወይም የፖለቲካ ድርጅት በመጀመሪያ ቅሬታዉን ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እንደሚችል ቀጥሎም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል እና በመጨረሻም ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ከእጩ ምዝገባ ጋር የተያያዘ በክልል የሚነሳ ክርክር የመጨረሻ ዉሳኔ የሚያገኘዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሆኑን ነዉ፡፡ነገር ግን በአ/አ/ ከተማ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ክልል ዉስጥ የሚገኙ ምርጫ ክልሎች ላይ ከእጩ ምዝገባ ጋር ተያያዞ የሚነሱ ክርክሮች በይግባኝ ለየትኛዉ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ የሚለዉ በዚህ ድንጋጌ ስር በግልጽ ያልተመለከተ ቢሆንም ከአዋጁ አንቀጽ 151/14 -16/ ድንጋጌ ጋር በማገንዘብ መረዳት እንደሚቻለዉ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑና በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለይም እጩ ምዝገባ በተመለከተ የሚሰጥ ዉሳኔ የመጨረሻ መሆኑን



17/09/13

ነዉ፡፡በሌላ በኩል የመራጮች ምዝገባ ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ ክርክሮች እንደአግባብነቱ በክልል ወይም በፌደራል ፍርድ ቤቶች በይግባኝ እንደሚቀርቡ የአዋጁ አንቀጽ 152/8/ ላይ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን የእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ በክልሎች ደረጃ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ይግባኝ ሰሚ እንደሆነ ተገልጾ የአ/አ/ ከተማ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን በሚመለከት በግልጽ አለመጠቀሱ በህገ መንግስቱ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቻ ስልጣን የተሰጠዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዳያየዉ የሚያደርግ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/ይመለከታል፡፡በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል የቀረበ የተለየ መከራከሪያ አለመኖሩን ልብ ይለዋል፡፡ጉዳዩም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ መርምሮ የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጥቶበታል ተብሎ ነዉ፡፡ከላይ እንደተመለከትነዉ ሌላ የይግባኝ እርከን ስለመኖሩ በህጉ ያልተመለከተ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ተብሎ ይወሰዳል፡፡የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ከተባለ ማናቸዉም የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን አቤቱታዉን ለሰበር ችሎት ማቅረብ እንደሚችል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም አሁን የቀረበዉን አቤቱታ ሰበር ችሎቱ መርምሮ ለመወሰን ከህግ የመነጨ ስልጣን ያለዉ መሆኑን በመገንዘብ ተጠሪ ያቀረበዉ ተቃዉሞ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

በመቀጠል አቤቱታ የቀረበበት ስረ ነገር ጉዳይ እንመለከታለን፡፤ከላይ እንደተገለጸዉ አከራካሪዉ ጉዳይ ስማቸዉ ከላይ የተገለጹት ሰዎች እጩነት በቀረቡበት ምርጫ ክልል ሊመዘገቡ አይችሉም ተብሎ መከልከላቸዉ ህጋዊ መሰረት አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን ይመለከታል፡፡በዚህ ረገድ አንድ ተወዳዳሪ በእጩነት ለመመዝገብ ማሟላት የሚገባቸዉ መስፈርቶች እንዲሁም በእጩነት እንዳይመዘገብ የሚከለክሉ ሁኔታዎች ምንድን ናቸዉ የሚለዉን መመርመር አስፈላጊ ነዉ፡፡በኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 31 ስር በዝርዝር እንደተመለከተዉ በእጩነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች ተብለዉ የተገለጹት ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆን፣እድሜ 21 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እና በሚወዳደርበት ምርጫ ክልል ነዋሪ ወይም ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሰራ መሆን እና የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ መቀበሉን በፊርማዉ ማረጋገጥ ከቻለ በእጩነት ለመመዝገብ ብቁ ነዉ ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 32/1/ሀ-መ እና ሰ ይመለከታል፡፡በሌላ በኩል ተወዳዳሪዉ



17/09/13

እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ ቢገኝ እንኳን በእጩነት ሊመዘገብ የማይችለዉ በህጉ የተመለከቱት ክልከላ ምክንያቶች መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ይህም በህግ ወይም በፍርድ ቤት ዉሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ የተገፈፈ ወይም በአእምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለዉ መሆኑ ስልጣን ባለዉ አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ከሆነ በእጩነት ሊመዘገብ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡አንቀጽ 31/1/ ንኡስ አንቀጽ ሠ እና ረ ይመለከታል፡፡ይህም የሚያሳየን በእጩነት ለመመዝገብ የሚቀርብ ሰዉ መስፈርቶቹን ማሟላቱን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን በሌላ በኩል ተወዳዳሪዉ በእጩነት ሊመዘገብ አይችልም የሚል ወገን በህጉ የተመለከቱት ክልክላ ምክንያቶች ስለመኖራቸዉ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በእጩነት ያቀረባቸዉ ሰዎች እንዳይመዘገቡ የተከለከሉት በወንጀል ጉዳይ ተከሰዉ በዋስ የመፈታት መብታቸዉን ተነፍገዉ በማረሚያ ቤት የሚገኙ ናቸዉ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ይሁንና የተባለዉ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 31/1/ ስር ለእጩነት እንዳይመዘገቡ ክልከላ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ሆኖ በግልጽ አልተመለከተም፡፡በሌላም በኩል እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየት የሚገባዉ ከምርጫ ህጉ ዓላማ አንጻር መሆን እንደሚገባ ይታመናል፡፡እንደሚታወቀዉ የዲሞክራሲያዊ መንግስት ስርዓት አንዱ መገለጫ የመንግስት ስልጣን የሚያዘዉ በምርጫ በመሆኑ ነዉ፡፡ ምርጫዉ ዲሞክራሲያዊ ነዉ ሊባል የሚችለዉ ተቀባይነት ያላቸዉ የምርጫ መሰረታዊ መርሆችን አሟልቶ ሲገኝ እና በዚሁ አግባብ ሲፈጸም ነዉ፡፡ይህም ማለት ማንኛውም ዜጋ ያለምክንያታዊ ልዩነት በቀጥታ ወይም በነፃነት በተመረጡ ተወካዮች አማካይነት በሕዝብ ጉዳዮች እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ፣ በእውነተኛ፣ ወቅታዊ፣ ሁሉን አቀፍ እና በእኩል አሳታፊ ሆነው በሚከናወኑ እና በመራጮች ፈቃድና በነፃነት የመግለጽ መብት ዋስትናን በሚሰጡ ምርጫዎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብትና ዕድል ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ ቅቡልነት ያገኙ መሰረተ ሃሳቦች ናቸዉ፡፡(ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 21 እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 25 ይመለከታል)፡፡ሀገራችን እነዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተቀበለችና ያጸደቀች መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 38 ላይ በዝርዝር እንደተገለጸዉም ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ልዩነት ሳይደረግበት በማንኛዉም የመንግስት ደረጃ በየጊዜዉ በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዳለዉ፣ምርጫም ሁሉ አቀፍ፣በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ

17/09/13

አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት እንደሆነ ለዚህም ህግ ዋስትና እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባዉ የህግ ማእቀፍ በኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 5 ላይ የተደነገገዉ ምርጫ የሚመራበትን መሰረታዊ መርሆዎች የሚመለከት ነዉ፡፡ምርጫዉ የሚመራበት መርህ ሆኖ ከተቀመጠዉ ዉስጥ አንዱ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አከባበር የሚመለከተዉ ሲሆን በአንቀጽ 5/2/ ስር እንደተገለጸዉ **<u>የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ያልተገደበ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ መምረጥ ወይም መመረጥ ይችላል፡፡</u>(ሰረዝ የተጨመረበት)**፡፡ከዚህ መርህ የምንገነዘበዉ ጉዳይ መምረጥ ወይም የመመረጥ መብት የዜጎች መሰረታዊ መብት ስለመሆኑ ገዥ የሆነ መርህ መሆኑን በሌላ በኩል ይህ መብት ሊከለከል ወይም ሊነፈግ የሚችለዉ በልዩ ሁኔታ በህግ ወይም በፍርድ ዉሳኔ ብቻ ስለመሆኑ ነዉ፡፡በህግ የተደረገ ክልከላ ነዉ የሚያሰኘዉ ህግ አዉጪዉ አካል አስቀድሞ ምክንያታዊና ተገቢ ናቸዉ ብሎ ያስቀመጣቸዉን መመዘኛዎችን ያላሟላ ወይም በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች በግልጽ መብቱ የተገደበበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን በፍርድ መብቱ የተገፈፈ የሚባለዉ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ ፍርድ ቤት አስቀድሞ በተሰጠ ፍርድ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ጨምሮ ሌሎች ህዝባዊ መብቶቹን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለዘወትር እንዳይጠቀም በፍርድ መብቱ የተሻረበትን ሰዉ የሚመለከት መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡በዚህ ረገድ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 123-124 እንደተነገዉ ከዝባዊ መብት መሻር እንደተጨማሪ ቅጣት የሚወሰድ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ የወንጀሉን ክብደት እና የጥፋተኛዉን ባሕርይ በማመዛዘን የሚወስነዉ መሆኑን ነገር ግን የሞት ቅጣት ወይም የጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት ሲሆን ፍርዱ ከመብት መሻርን በተጨማሪነት ሊወሰን እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡(የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ 1997ዓ.ም) ይመለከታል፡፡ስለሆነም በፍርድ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት የሚሻረዉ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እና ተጨማሪ ቅጣት ሆኖ ዉሳኔ ሲሰጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮች ልምድ ሲታይ የመመረጥ ወይም የመምረጥ መብት ላይ ገደብ የሚደረገዉ በህግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ስለመሆኑ እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ በመመዘኛነት የሚወሰደዉ እጩ ተመዝጋቢ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ በፍርድ የተረጋገጠ(convicted) ወይም የቀደመ የወንጀል ሪኮርድ(criminal record) መኖር አለመኖሩን በመመርመር ነዉ፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
17/09/13

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ያቀረባቸዉ እጩዎች በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸዉ በክርክር ሂደት ላይ ስለመሆናቸዉ እንጂ ጥፋተኛ ተብለዉ በፍርድ ህዝባዊ መብታቸዉ የተሻረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡በእርግጥ በወንጀል ጉዳይ የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት በዋስትና የመፈታት መብታቸዉ የተከለከሉ ከሆነ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብታቸዉ ላይ ገደብ መደረጉን ያሚያል፡፡ሆኖም የጥፋተኛነት ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ያላቸዉ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20/3/ ይመለከታል፡፡የዚህ ድንጋጌ ዋነኛ ዓላማ የማስረጃ አቀራረብ እና የማስረዳት ሸክም የዓቃቤ ህግ መሆኑን ያሳያል ሲል የሥር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ምክንያት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ተከሳሹ በህግ በግልጽ ያልተከለከሉ ወይም ያልተገደቡ መብቶቹንም ጭምር እንዳይነኩበት የመከላከል ዓላማ እንደያዘ መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡የመምረጥ እና የመመረጥ መብቱም ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት የሚገባዉ ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ በወንጀል ክስ ቀርቦባቸዉ በክርክር ሂደት ላይ ያሉ ሰዎች በእጩነት እንዳይመዘገቡ በግልጽ ክልከላ ስለመደረጉ የአዋጁ አንቀጽ 31/1/ ድንጋጌ ስር አልተመለከተም፡፡በመሆኑም በህግ ወይም በፍርድ መብታቸዉ የተገደበ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡

ሌላዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ምክንያት ሰዎቹ በህግ ጥላ ስር ያሉና የመንቀሳቀስ መብታቸዉ የተገደበ ስለሆነ በእጩነት ቢመዘገቡ ህዝቡን በአካልም ሆነ በሚዲያ ሊያገኙ አይችሉም የሚል ነዉ፡፡የእጩ አቀራረብና ምዝገባ በተመለከተ በምርጫ አዋጁ እንደተደነገገዉ ማንኛዉም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫ አዋጁ የተመለከተዉን መስፈርት የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር እንደሚችል እና እጩ በአካል መቅረብ ካልቻለ እጩዉን ያቀረበዉ የፖለቲካ ፓርቲ አግባብነት ያለዉን ማስረጃ አቅርቦ እጩዉን ማስመዝገብ እንደሚችል ያመላክታል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 32/1/ እና 6 ይመለከታል፡፡ከዚህም ሌላ በአካል መቅረብን አስገዳጅ ያደረገዉ ድምጽ ለመስጠት የሚቀርብ መራጭ በሚመለከት ስለመሆኑም ከአዋጁ አንቀጽ 5/4/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ሌላዉ የምርጫ ቅስቀሳን በተመለከተም እጩ ተወዳዳሪዉ በፖለቲካ ፓርቲ በኩል የቀረበ ከመሆኑ አኳያ የምርጫ ቅስቀሳ ስራ የሚሰራዉ በዋናነት ፓርቲዉ በኩል መሆኑን መገንዘብ አስቸጋሪ ካለመሆኑም በተጨማሪ በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክር በሌለበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ለዉሳኔ ምክንያት ማድረጉ ተገቢነት የለዉም፡፡ይህንኑ የሚያጠናክረዉ ሌላዉ ምክንያት የመምረጥ መብታቸዉ ያልተገደበ ነገር ግን በወንጀል ተከሰዉ ወይም



17/09/13

ጥፋተኛ ተብለዉ በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሆነዉ መምረጥ እንዲችሉ በልዩ ሁኔታ እንዲመቻችላቸዉ አዋጁ ላይ በግልጽ መደንገጉ ነዉ፡፡አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 17/1/ይመለከታል፡፡ይህም የሚያሳየን የምርጫ ህጉ የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ (poltical particpation) ትኩረት መስጠቱን እና የሚያበረታታ መሆኑን ነዉ፡፡

በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበዉ ሌላዉ መከራከሪያ ለአቤቱታ ምክንያት በሆኑት የምርጫ ክልሎች ላይ አመልካች ተተኪ እጩዎችን አቅርቦ አስመዝግቧል የሚል ሲሆን በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የቀረበ ክርክር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡አመልካችም በመልስ መልሱ ላይ በግልጽ ምላሽ አልሰጠበትም፡፡በመሰረቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 329/1 እንደተደነገገዉ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ የፍሬነገር ክርክር በበላይ ፍርድ ቤት ሊነሳ እንደማይችል እና ፍርድ ቤቱም ዉሳኔ ሊሰጥበት እንደማይገባ ተመልክቷል፡፡በሌላም በኩል የተባለዉ ፍሬነገር በእዉነት የተፈጸመ ስለመሆኑ ከማስረዳት አኳያ የተመዘገቡት ተተኪ እጩዎች ማንነት እና ምዝገባዉ የተደረገበት ጊዜ ጭምር ይህን ችሎት በሚያሳምን ሁኔታ ተጠሪ በመልሱ ላይ የገለጸዉ ነገር የለም፡፡በዚህ ምክንያት ተጠሪ በአማራጭ ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

ሲጠቃለል በህገ መንግስቱም ሆነ በምርጫ ህጉ ቅቡልነት ያገኙት መርሆዎች የዜጎች በመምረጥም ሆነ በመመረጥ የመሳተፍ መብታቸዉ የተከበረ ስለመሆኑና ይህ መብት ሊገደብ የሚችለዉ በህግ በተገለጹት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን የምያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ስለዚህም በምርጫ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ምርጫ ህጉ ሊተበገር የሚገባዉ ጠቅላላ ምርጫዉን ምሉእ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ማድረግን ታሳቢ አድርጎ የወጣ የምርጫ ህግ ዓላማና መንፈስ በመከተል እና የዜጎችን ተሳትፎ የሚያበረታታ እንዲሆን በማድረግ የሚያስችል መደላድል የሚፈጠር ሊሆን ይገባል፡፡በመሆኑም አመልካች ያቀረባቸዉ እጩዎች በወንጀል ጉዳይ ተከሰዉ በህግ ጥላ ስር በመሆናቸዉ ብቻ በእጩነት እንዳይመዘገቡ የምርጫ ህጉ ግልጽ ክልከላ ባላደገበት ሁኔታ ወይም በፍርድ የመምረጥና የመመረጥ መብታቸዉ መገፈፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በእጩነት እንዳይመዘገቡ በምርጫ ክልሉ አስፈጻሚ አካል የተሰጠዉ ዉሳኔ እና በየደረጃዉ ባሉት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የጸናዉ ዉሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 31/1/ሠ እና የምርጫ ህጉን መሰረታዊ መርሆዎችና ዓላማ ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥናል፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

17/09/13

<u>ውሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ አመልካች ያቀረባቸዉ እጩዎች አቶ እስክንድር ነጋ፣አቶ ስዩም ቸኮል እና ወ/ሮ ቀለብ ስዩም በቅደም ተከተል በየካ ክ/ከ/፣በንፋስ ስልክ ላ/ክ/ከ እና በምርጫ ክልል 26/27 በተወዳዳሪነት ሊመዘገቡ አይገባም ተብሎ በየምርጫ ክልሎቹ የተሰጠዉ ዉሳኔና በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የጸናዉ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/268967 ላይ በ26/07/2013ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/አመልካች ያቀረባቸዉ እጩዎች በእጩነት እንዳይመዘገቡ የሚከለከሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡በዚሁ መሰረት እንዲፈጸም ከላይ ለተገለጹት ምርጫ ክልሎች ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፊርማ ቀን 17/09/13